የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራሁለተኛ ዓመት ቁጥር ፳፮
አዲስ አበባ ግንቦት ፴ ቀን ፲፱፻፺፰

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

12th Year No. 26
ADDIS ABABA 7th June, 2006

<u>ማውጫ</u>

አዋጅ ቁጥር ፬፻፺፩/፲፱፻፺፰ ዓ.ም

ለሀገረ ማርያም ሜጋ የኃይል ማስፋፊያ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከሕንድ የኤክስፖርት ኢምፖርት ባንክ ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ... ገጽ ፫ሺ፬፻፲፪

<u>CONTENTS</u>

**Proclamation No. 491/2006**

Export Import Bank of India Credit Line Agreement for the Hagere Mariam-Mega Power Transmission Project Ratification Proclamation.... Page 3412

## አዋጅ ቁጥር ፬፻፺፩/፲፱፻፺፰ ዓ.ም

### በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በሕንድ የኤክስፖርት ኢምፖርትባንክ መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ <u>አ ዋ ጅ</u>

ለሀገረ ማርያም ሜጋ የኃይል ማስፋፊያ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል መጠኑ ፷፭ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር /ስድሳ አምስት ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር/ የሆነ ገንዘብ የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በሕንድ የኤክስፖርት ኢምፖርት ባንክ መካከል እ.ኤ.አ. አፕሪል ፳ ቀን ፪ሺ፮ በኒው ዴልሂ የተፈረመ በመሆኑ፣

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ግንቦት ፲፭ ቀን ፲፱፻፺፰ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው ስለሆነ፣

በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና /፲፪/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል::

**፩. <u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ አዋጅ "ለሀገረ ማርያም ሜጋ የኃይል ማስፋፊያ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከሕንድ የኤክስፖርት ኢምፖርት ባንክ ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፬፻፺፩/፲፱፻፺፰" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

## PROCLAMATION NO. 491/2006.

### A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE EXPORT-IMPORT BANK OF INDIA

**WHEREAS,** a Loan Agreement, between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Export Import Bank of India stipulating that the Export Import Bank of India provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a Loan in an amount not exceeding 65,000,000 USD (sixty five million United States Dollars) for financing Hagere Mariam-Mega Power Transmission Project, was signed in New Delhi on the 20th day of April 2006;

**WHEREAS,** the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Loan Agreement at its session held on the 23rd day of May, 2006;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55 Sub-Article (1) and (12) of the Constitution it is hereby proclaimed as follows:

**1. Short Title**

This Proclamation may be cited as the "Export Import Bank of India Credit Line Agreement for the Hagere Mariam-Mega Power Transmission Project Ratification Proclamation No.491/2006."

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 2.30

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

**፪. የስምምነቱ መፅደቅ**

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በሕንድ ኤክስፖርት ኢምፖርት ባንክ መካከል እ.ኤ.አ. አፕሪል ፳ ቀን ፪ሺ፮ የተፈረመው የብድር ስምምነት ፀድቋል::

**፫. የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትሩ ሥልጣን**

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትሩ በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፷፭ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር /ስድሳ አምስት ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር/ በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል::

**፬. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል::

አዲስ አበባ ግንቦት ፴ ቀን ፲፱፻፺፰ ዓ.ም.

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**2. Ratification of the Agreement**

The Loan Agreement signed in New Delhi on the 20th day of April 2006 between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Export-Import Bank of India is hereby ratified.

**3. Power of the Minister of Finance and Economic Development**

The Minister of Finance and Economic Development is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the loan amount of 65,000,000 USD (sixty five million United States Dollars) in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan Agreement.

**4. Effective Date**

This Proclamation shall enter into force on the date of its publication in the Federal Negarit Gazeta.

**Done at Addis Ababa, this 7th day of June, 2006**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት